THE GEORGE WASHINGTON UNIVERSITY
WASHINGTON, DC

# የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የአቅራቢ ምዝገባ ቅጽ

## የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የአቅራቢዎች መመሪያ (GW)

አብዛኞቹ በአሜሪካ የሚገኙ አቅራቢዎች የአቅራቢነት ምዝገባ ጥያቄያቸውን በGW iSupplyGW Portal በኩል ማቅረብ አለባቸው፡፡ አለም አቀፍ ወይም የተመረጡ የሀገር ውስጥ ግለሰቦች፤ ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች ከሆኑ አቅራቢዎቹ አስፈላጊ ቅጾችን ሞልተው ሲመዘገቡ የግዢ ትዕዛዞች እና/ወይም ክፍያዎች የሚላክላቸው ይሆናል፡፡ ሽልማቶችን፣ የጉዞ የቅድሚያ ክፍያዎችን ወይም ካሳዎችን  የሚያገኙ ተማሪዎችና ሰራተኞች የአቅራቢዎች የምዝገባ ቅጾችን ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡

## የተሸፈነ አቅራቢ

- የተመረጡ የሃገር ውስጥ ግለሰቦች፤ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች
- ዓለም አቀፍ ግለሰቦች፤ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች

## ቅጾች

ማናቸውም የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ግለሰቦች፤ኩባንያዎች ወይም ድርጅቶች አገልግሎቶችን ወይም እቃዎችን ለGW ከማቅረባቸው በፊት የሚከተሉትን ቅጾች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡

- የአቅራቢ ምዝገባ ቅጽ፤ የባንክን ጨምሮ
- IRS ለW-9፤ ለአገር ውስጥ አቅራቢዎች በቅጹ ላይ ያሉት ሁሉም ክፍሎች የሚያስፈልጉ ሲሆን ፊርማና ቀን ሊኖረው ይገባል፡፡ የቅጽ መመሪያውን በመመልከት የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

  (ወይም)
- IRS ቅጽ W-8BEN ወይም W-8BEN-E፤  ለዓለም አቀፍ አቅራቢዎች፤ ፊርማና ቀን ሊኖረው ይገባል፡፡ የቅጽ መመሪያውን በመመልከት የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

## የመላኪያ መንገዶች

- ኢ-ሜይል ፡ iSupplyGW@gwu.edu
- ፋክስ፡ 571-553-8523
- እርዳታ ለማግኘት ሲፈልጉ፡ 571-553-0300
- ለተጨማሪ መረጃ ድህረ-ገጻችንን ይጎብኙ

## የአቅራቢው የዲይቨርሲቲ ተነሳሽነት ፕሮግራም (MBE / WBE)

ትኩረት ያልተሰጣቸው ግለሰቦችንና የሴቶችን ተሳትፎ (MBE / WBE) ለመጨመር ያስቀመጠውን እቅድ ያግዝ ዘንድ ዩኒቨርሲቲው በፈቃደኝነት **“የአቅራቢዎች የዲይቨርሲቲ  ተነሳሽነት ፕሮግራም”** ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ GW ይህን ዓላማ በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ አቅራቢዎች በኩል ከግብ ለማድረስ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ አቅራቢዎች እነዚህን ትኩረት ያልተሰጣቸውን ግለሰቦችንና ሴት አቅራቢዎችን በምን ዓይነት መልኩ ሊያግዙ እንደሚችሉ የሚገልጽ ዕቅድ ከሚልኩት ሰነድ ጋረ አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ እቅድ በታማኝነትና በቅን-ልቦና የሚገመገም ሲሆን የሚከተሉት ነጥቦች ከግምት ውስጥ የሚገቡ ይሆናል፡

- በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠቀሱትን እቃዎችና አገልግሎቶች ማቅረብ የሚችሉ ትኩረት ያልተሰጣቸውን ግለሰቦችንና ሴቶች መኖር አለመኖራቸው፤
- እጩ የሁለተኛ-ደረጃ አቅራቢዎች ተወዳዳሪነት

በከተማችን የሚገኙ ትኩረት ያልተሰጣቸውን ግለሰቦችንና የሴቶችን የንግድ ተጠቃሚነት በማሳደግ ከማህበረሰቡ ጋር ያለንን ቁርጠኝነት ማጠናከር እንችላለን፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ ሻጮች ከዋጋ፤ ከአገልግሎት አሰጣጥ እና ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ የተቀመጠውን መስፈርት ያሟላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ የአቅራቢዎች ስብጥር እንደ አንድ መስፈርት ቢጠቀስም ጨረታውን ለማሸነፍና የስራ ውል ለመፈራረም ብቸኛ ታሳቢ ጉዳይ አይሆንም፡፡ የመጀመሪያው አቅራቢ የትኛውን ሁለተኛ ደረጃ አቅራቢ መጠቀም እንዳለበት ራሱ የሚወስን ይሆናል፡፡ ውሉ በሚሰጥበት ወቅት የመጀመሪያው አቅራቢ የስራ ክንውኑን ከሁለተኛ አቅራቢው በየወሩ በመሰብሰብ ሂደቱን መከታተል ይኖርበታል፡፡

THE GEORGE WASHINGTON UNIVERSITY
WASHINGTON, DC

# የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ የአቅራቢ ምዝገባ ቅጽ

## ይህን ቅጽ ለመሙላት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ይጠቀሙ

### አቅራቢው መረጃ

| ንግድ / የግል ስም | | | የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር (EIN ወይም SSN) |
|---|---|---|---|
| የመልዕክት አድራሻ (የግብር ቅጽ የተለየ ከሆነ) | ከተማ | ክልል / አገር | አካባቢያዊ መለያ ቁጥር |

### የመገኛ አድራሻ

| ለመቀበል የሚቻሉ አካውንቶች | ስልክ | ፋክስ | ኢ-ሜይል |
|---|---|---|---|
| የሽያጭ አድራሻ | ስልክ | ፋክስ | ኢ-ሜይል |

### የGW አድራሻ

| የስራ ክፍል ተጠሪ ስም | የስራ ክፍል ኢ-ሜይል አድራሻ |
|---|---|

### ውሎች እና የክፍያ መረጃ

ነባሪ የክፍያ ውል: የተጣራ 30

የዋጋ ቅናሽ ማድረጊያ ስምምነቶች ካሉ ይዘርዝሩ ________________

ደረሰኞችን ወደ invoice@gwu.edu ይላኩ (ወይም)

University Payables
45155 Research Place
Suite 360
Ashburn, VA 20147

ለተጨማሪ ጥያቄዎች: P2P@gwu.edu ወይም 571-553-0247 ይደውሉ

**የክፍያ ዘዴዎች**

- ☐ ACH (ተመራጭ)
- ☐ Wire
- ☐ Check

### ACH ወይም Wire የአከፋፈል መመሪያዎች

| | |
|---|---|
| ባንክ ወይም የገንዘብ ተቋም ስም | |
| ባንክ መለያ ስም | |
| ስዊፍት / ማስተላለፊያ ቁጥር | |
| የባንክ ሂሳብ ቁጥር | |
| መላኪያ ኢ-ሜይል አድራሻ | |

GW እና ከላይ የተጠቀሰው የፋይናንስ ተቋም በስምምነቱ መሰረት ክፍያዎችን አውቶማቲካሊ እንዲፈጸሙ እኔ / እኛ በፊርማዬ/ችን አረጋግጣለሁ/እናረጋግጣለን:: ይህ ስምምነት መሰረዙን በጽሁፍ እስካላሳወኩ/ቅን ድረስ ውሉ ተግባራዊ ይሆናል::

### የአቅራቢው ፊርማ

| ፊርማ | የስራ መደብ | ቀን |
|---|---|---|

እባክዎ የተጠናቀቀውን የአቅራቢዎች ምዝገባ ቅጽ እና አግባብነት ያላቸውን የግብር ቅጾች ወደ iSupplyGW@gwu.edu ይላኩ::
እርዳታ ለማግኘት iSupplyGW ቡድንን በዚህ ስልክ ቁጥር ደውለው ያነጋግሩ: 571-553-0300 ወይም ወደ iSupplyGW@gwu.edu ኢ-ሜይል ይላኩ::